የኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ (ኢፖእአኮ)
SOLIDARITY COMMITTEE FOR ETHIOPIAN
POLITICAL PRISONERS (SOCEPP)

**ግንቦት** 3/ 2001

**<u>ለኢትዮጳያውያን ሁሉ መልዕክት</u>**

**<u>ሁሉም የፖለቲካ እስረኞች እንዲፈቱ እንታገል</u>**

**በ ግንቦት- ሰኔ 1997 ብዙ መቶ ኢትዮጵያውያን በአረመኔው ወያኔ ሲፈጁ ብዙ ሺዎች ደግሞ ወደ ዴዴሳ፤ ብር ሸለቆ ፤ ሸዋ ሮቢት ፤ ዝዋይ ና ሌሎች እስር ቤቶች ተወስደው እስከዛሬ በመሰቃየት ላይ ናቸው፡፡ እነ እገሌ እነ እገሌ ታሰሩ ተብሎ በመታወቃቸው ስማቸው እየተጠራ ይፈቱ የሚባልላቸው ያሉ ሲሆን ብዙ ሺዎች ደግሞ ማንነታቸው ባይነሳም ለሕዝብና ለሀገር ሲሉ መከራና ፍዳን እየተቀበሉ በመሆናቸው ይፈቱ ብለን ልንታገልና ልንጮህላቸው ይገባናል፡፡**

**ሰብዓዊ መብት ስንል ለተወሰኑት ብቻ በሚል ሊሆን አይችልም፡፡ አንዳንድ ራሳቸውን የሰብዓዊ መብት ጠበቃ እያሉ ግን እስረኛ ከእስረኛ የሚለዩና በፖለቲካና ሌላ አቅዋም የተነሳ ልዩነትን የሚፈጥሩና በዚያውም ዝምታን የሚመርጡ አሉ፡፡ ይህ መቆም መቀየር ያለበት ነው ፡፡ የወያኔ አገዛዝ በተለመደ አጓጉል ብልጠቱ በየጊዜው የመጮሂያ ርዕስ ሲሰጠን በዚያው መሰረት ሌላውን እየረሳን በተቀደደልን ቦይ ብቻ መፍሰሱን ማቆም ይኖርብናል፡፡ በባዕድ ሀገር ኢትዮጵያውያን ለምሳሌ የታሰሩ ይፈቱ ብለው ሲሰለፉ የተወሰኑ ታዋቂ ወይም የዛሬ ዛሬ ታሳሪዎችን ብቻ ስም በማንሳትና ፎቶ/ምስል በማውለብለብ ሲጮኹ በርካታ ጊዜ አይተናል፡፡ ለእስር ተዳርገው ለዓመታት የሚማቅቁት እነ አቶ አበራ የማነ አብ፤ ደብዛቸው የጠፉው እነ ፀጋዬ ገብረመድህን፤ ተይዞ የት እንደደረሰ የማይታወቀው ጋዜጠኛ ብርሃኑ እጅጉ፤ አስተማሪ ኢዮብ፤ ሰራቶኛ ማህበር መሪ አበበ ዓይነኩሉ፤ታጋይ ሻለቃ አዱኛ፤ ወዘተ ከቶም ስማቸው አይነሳም፡፡ በከርቸሌ ቃሊቲ የታሰሩት 120 ታዋቂ የፖለቲካ ሰዎችና ጋዜጠኞች ከተፈቱ በኋላ በየማጎሪያው የተጣሉትና መከራ የሚቀበሉት 35 ሺ በላይ እስረኞች ተረስተዋል ቢባል ስህተት አይሆንም፡፡ በህገር ሽማግሌ ጭምብል ጀርባ የወያኔን አገዛዝ ፖለቲካ የሚየራምዱትም ቢሆኑ ስለነዚህ ሲያነሱ ሰምተን አናውቅም፡፡ ባይረሱማ ኖሮ በመጪው ምርጫ ለመሳትፍ ደፋ ቀናው ሲታይ በዚያውም የታሰሩት ካልተፈቱ የሚል ቅድመ ሁኔታ ሲቀርብ ለመስማት በቻልን ነበር፡፡ የወያኔ አገዛዝ በአዲስ አባባ ሳይቀር በምስጢር እስር ቤቶች ብዙ ዜጎችን እየገረፈና እያሰቃየ እንዳለ እናውቃለን፡፡ አማራ ኦሮሞ ወዘተ እያለ በየቦታው ብዙ ሺ አግቷል፡፡ በጋምቤላ፤ በኦጋዴን ወዘተ ፍጅት ማካሄድ ብቻ ሳይሆን በየእስር ቤቱ ብዙዎቹን ከቶ እያሰቃየ ነው፡፡ እነዚህን ሁሉ በማስታወስና በመጥቀስ ይፈቱ ብለን መጮህ መቻል አለብን አንጂ ለተወሰኑት ብቻ ተቆርቋሪ ሆኖ መቀጠሉ ለትዝብት ለመዳረጉ ሌላ የሚወገዝም ይሆናል፡፡**

**ሁሉም የፖለቲካ እስረኞች ይፈቱ ፡፡ ይህን ጩኸት ለማሰማት ከታሰሩት ጋር በፖለቲካ አቅዋም መስማማት የለብንም፡፡ ፍትህ ሲጓደልና በህገወጥ መንገድ ማንም ዜጋ ሲያዝና መብቱ ሲረገጥ መቃወም መቻል አለብን፡፡**

**ሁሉም የፖለቲካ እስረኞች ይፈቱ!!**


INJUSTICE ANYWHERE IS INJUSTICE EVERYWHERE

SOCEPP, POSTFACH 51213, BERLIN 13372,GERMANY

SOCEPP, 30 RIGA COVE, WINNIPEG,MB R2P 2Z7,CANADA

E MAIL: SOCEPP @AOL.COM

WEB SITE: WWW.SOCEPP.DE